# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ ማሳሰቢያ

ጥቅምት20 ቀን 2001 ዓ/ም (ኦክቶበር 30 ቀን 2008 ዓ/ም)

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር (ኢሕአግ) አለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴን በመወከል አቶ ስለሺ ጥላሁን ባለፉት ሶስት ሳምንታት ወደ ግንባሩ ጉዞ በማድረግ ከአርበኞችና ከአርበኞች የአመራር አካላት ጋር ለድርጅቱ ጠቃሚ የሆኑ ውይይቶች አድርገዋል፡፡ በኤርትራም ከተለያዩ የሚመለከታቸው ባለስልጣናት ጋር ግንባሩንና ያገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በተመለከተ ግልፅ ውይየት በማድረግ ለድርጅታችንም ሆነ ለሃገራችን ጠቃሚ የሆኑ ስራወች አከናውነዋል፡፡ በቆይታቸው ጉብኝታቸውን አስመልክቶ ስላደረጉት የስራ ክንውኖችና ተያያዥ ጉዳዮችን በሚመለከት፤ ላባላቶቻችን፤ ደጋፊዎቻችንና ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ደረጃውን የጠበቀ ማብራሪያ በተለያዩ የመገናኛ በዙኃን እንዲሰጡ መመሪያ የሰጠን መሆኑን ስንገልፅ፤ በአካል በመገኘት በፅናት ለግንባሩ በመቆም ስላደረጓቸው የስራ ክንውኖች፤ በዚህ አጋጣሚ በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስም፤ ውጭ በምትገኙ አባላቶችና ደጋፊዎቻችን ስም ምስጋና ልናቀርብላቸው እንወዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ሊቀመንበር

አርበኛ መአዛ ጌጡ

**አንድነት ሐይል ነው!**
**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር!**